# ዓለም አቀፍ የወባ በሽታ ድርጅት
# MALARIA FOUNDATION
## I N T E R N A T I O N A L

*ለዓለም ሁሉ ሰብአዊ እርዳታን የሚያዳርስ*

አላማችን በወባ በሽታ በሚመጡ የጤና፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ችግሮች መፍትሄ ማፈላለግ እና መፍትሄዎቹም እንዲበለጽጉ እና በስራ ላይ እንዲውሉ ማመቻቸት ነው።

.



### የአመራር እድገት

MFI/ ዓወድ ወባን ለመከላከል የሚውለው ውይይት፣ ምክክር እና ክርክር ስልትን በመጠቀም ዓለም አቀፋዊ አመራርን እና ወዳጅነትን ያበለጽጋል። የግንኙነት መረባችን ተማሪዎችን፣ አስተማሪዎችን፣ ተመራማሪዎችን፣ የንግድ ሰዎችን እና የአካባቢ ሽማግሌዎችን ያካትታል።.



### ህብረተሰቡን ማስተማር

MFI/ዓወድ በአካባቢ ሽማግሌዎች እና በልጆች ላይ የሚካሄደውን ትምህርት እና የድጋፍ እንቅስቃሴ ያበረታታል። በወባ በሽታ በሚጠቁ ቦታዎች ላይ ፕሮግራማችን ለሕበረተሰቡ ልዩ ግንኙነቶችን እና እድሎችን ይገነባል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ወባ በሌለበት አገር ያሉ ልጆች በዚህ በሽታ ምክንያት የመጣው ውድመት በቀላሉ ይሰማቸዋል።



### የወባ በሽታ እውቀት

ከ1992 ጀምሮ MFI/ዓወድ የወባ በሽታን ለመዋጋት ዓለም አቀፍ ጥረት እንደሚያስፈልግ በማሳወቅ ላይ ስርቷል። ዋና ዋና ውጤቶቹ የሚያካትቱት፡ የመጀመሪያውን በወባ በሽታ ላይ ያተኮረ ድህረ ገጽ ማስጀመር፣ የመጀመሪያውን የወባ መረጃ ያየዘ ፐሬስ ኪት ማዘጋጀት፣ የወባ በሽታን በመከላከል ሂደት ላይ የዲዲቲን አጠቃቀም የመገደብ ቅስቀሳ ላይ እና ዓለም ሁሉ ወደ አረትሚሲኒን ያተኮረ ቅልቅል ህክምና artemisinin-based combination therapy (ACT) እንዲያተኩር አቋም ይዞ መደገፍ።




### የምርምር ቅስቀሳ



ለጊዜው የዋባ በሽታን መከላከል እና ማከም የሚቻል ቢሆንም፣ የ MFI/ ዓወድ ተመራማሪዎች አዲስ ፍቱን መድሃኒት እና ክትባት ለማግኘት እና ስራ ላይ ለማዋል ቅስቀሳ እያኪያሄዱ ነው።

**እኛ ማን ነን**

የዓለም አቀፍ የወባ በሽታ ድርጅት MFI/ዓወድ የተመሰረተው በ 1992 በ ዶ/ር ሜሪ አር ጋሊንስኪ ነው። በወባ በሽታ ተመራመሪዎች እና በተለያየ የስራ ዘርፍ ላይ በተሰማሩ ባለሞያዎች ሙሉ ፍላጎት እና ቁርጠኝነት አማካኝነት አዓም አቀፋዊ የሆነ የግል ተቋም በመፍጠር ፍቱን የመከላከያ ዘዴ፣ ህክምና እና ወባ መቆጣጠሪያ ለማቋቋም የተነደፈው እቅድ ተግባራዊ ሆኗል። MFI/ዓወድ ይህንን ሁኔታ ከሚደግፉ በርከት ያሉ ግለሰቦች እና ቡድኖች ጋር በመተባበር ይሰራል።

**ወቅታዊ ዓለም አቀፍ ተነሳሽነት**



**የወባ በሽታ እንግታ - የሰማያዎ ሪባን ዘመቻ፡** በአትላንታ በ 2006 የአሜሪካ ትሮፒካል መደሃኒት እና ጽዳት ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ተጀመረ። የወባ በሽታን እንግታ - ሰማያዊ ሪቫን አለም የወባ በሽታን ለማጥፋት ለሚደረገው ትግል የቁርጠኝነት እና የቃል የመግባት ምልክት ሆኗል።

**የተማሪ መሪዎች ከወባ ጋር፡** ይህ ፕሮግራም ተማሪዎችን ስለ ወባ በሽታ በማስተማር እና በሽታውን በማጥፋት ሂደቱ ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ የተነደፈ ነው። ከ 2005 ጀምሮ የዚህ ፕሮግራም የሙከራ ሂደት በአሜሪካ፣ አፍሪካ እና እሲያ በመስፋፋት ላይ ነው።.

**አለም አቀፍ ቸሃ ኩዋንግ ዶ ማረሻል አርት (CKD)፡** ይህ ፕሮግራም ከ MFI/ዓወድ ጋር በመተባበር የወባ በሽታን ለማጥፋት በሚደረገው ጥረት ላይ እየተሳተፈ ነው። በአሜሪካ እና በታለቋ እንግሊዝ የሚገኙ የ CKD አስተማሪዎች እና ተማሪዎች የወባ በሽታን በተመለከተ የማሳወቅ፣ የማስተማር እና የኢኮኖሚ እድገት ቀሰቃሾች ሆነዋል። .

**የዋባ በሽታ ጉዳይ መሪነት ጉባኤ፡** የወባ በሽታ ባለሞያዎችን፣ የንግድ እና የማህበረሰብ መሪዎችን አገናኝቶ ስለ ወባ በሽታ አሰከፊ እውነታዎችን እንዲያውቁ እንዲሁም የባህር ውስጥ ጠላቂዎች ቡድን ወባ በሽታን በመወጋቱ ሂደት ላይ እንዴት ሊሳተፉ እንደሚችሉ አሰተምሯል።



**የወባ በሽታ ሽልማት በዓል፡** በ 2006 ተጀመረ፣ MAC/ዓወድ አስተማሪዎችን፣ ተማሪዎችን፣ ተመራማሪዎችን ጋዜጠኞችን፣ የንግዱ ማህበረሰብ መሪዎችን፣ ታዋቂ ሰዎችን እና ፖለቲከኞችን የሚጨምር የተለያዩ መሪዎችን አሰተዋጽዎ በመገንዘብ እነዚህን ጀግኖች ወባን በመዋጋቱ ሂደት ላይ እንዲሳተፉ አድርጓል፣

**በአሁኑ ጊዜ ስላሉት የ MFI's/ዓወድ ፕሮግራሞች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ እባክዎትን የመረጃ መረባችንን ይጎብኙ www.malaria.org, ወይም በ MFI@malaria.org ያነጋግሩን።**

**የትርጉም ስራ የተሰራው፡ www.worldvoicecenter.com**

**June 2009**